# የሀይማኖት አባቶች ዳግማዊ ሴራን እንደ “ታቦት” አጅበው ለመግባት መጠቀሚያ አይሆኑም

ከሀይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

አበው “ስደት ለወሬ ያመቻል አሉ” ብለው ተርተው ነበር። እውነት አላቸው። በሀገራችን በጦርነት፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በተፈጥሮ አደጋ፣ በተለያየ እምነት፣ በሀይማኖት ግጭት ወዘተ.. የተነሳ ካለው መንግሰት በመሸሽ ህይወታቸውን ከአደጋ ለማዳን የተወለዱበትን፣ ያደጉበትን፣ የሚወዱትን አገርና ህዝብ ጥሎ መሰደድ በጣም ከባድ ነገር ነው። አዎን ስደት እስኪለመድና መረጋጋት እስኪገኝ ድረስ ብዙ ፈተና፣ መከራ፣ ውጣ ውረድ የበዛበት ህይወት ነው ። እነዚህን መከራ፣ ፈተና፣ ችግር ለመቻል የሚመረጡበት ምክንያት ባለመሰደድ ከሚመጣው አደጋ የተሻለ ስለሆኑ ነው። ሌላው ደግሞ የቅንጦት “ስደተኛ” (ከሞትና ከአሜሪካ የሚቀር የለም ብሎ የወጣ)፣ ወንጀል ሰርቶ ከፍትህ በመሸሽ የወጣ “ስደተኛ” ፣ በ “ስራ” ስም ለስለላ የተላከ “ስደተኛ” ፣ የተዘረፈ ሀብትና ገንዘብ ይዞ የወጣ “ስደተኛ” ፣ ተቃዋሚ መስሎ ተቃዋሚውን ለመከፋፈል የተላከ “ስደተኛ” ወዘተ… እነዚህ ደግሞ የተለየ ዓላማ ይዘው በስደት ስም የሚነግዱ ናቸው። ስለሆነም “በተልዕኮ” የወጡትን ተቸግረው ከወጡት ለመለየት ቢያስቸግርም በሚሰሩት ተግባርና አካሄድ ይታወቃሉ።

በደርግ ጊዜ እስራቱና ግድያውን በመፍራት ህይወታቸውን ለማዳን በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተሰደው መኖር ከጀመሩ በሁዋላ በውጭ ያለው የስደተኛ ቁጥር እየጨመረ ውሎ አድሮ ደግሞ ቀሪ ቤተሰብ በማምጣትና በመዋለድ ቁጥሩ በያመቱ እየጨመረ መጥቶ፤ በዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ ዘመን ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠር ወጣት፣ አዛውንት፣ ምሁር፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ተቃዋሚዎች፣ ኑሮ የከበዳቸው፣ ዘረኝነት ያሰመረራቸው ሁሉ ስደተኛ ሆነዋል።

የሃይማኖት አባቶች ስደትን በተመለከተ፤ የአባ ጳውሎስ የኦርቶዶክስ ህይማኖት ቀኖናን በመጣስ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ተሹመው ቤተክርስቲያኒቱን ሲያምሱና ሲከፋፍሉ ደግሞ፣ የሀይማኖት አባቶች በብዛት መሰደድ ጀምረው በያሉበት አካባቢና ከተሞች ቤተክርስቲያን በማቋቋም፤ ፓትርያርኩ ብጹህ አባታችን መርቆሪዎስ ከተሰደዱ በሁዋላ፤ ጳጳሳቱና አባቶች አንድ ላይ በመሆን ስደተኛው ሲኖዶስን በማቋቋም፤ በህግ ታውቆ ምእመናኑን አገልግሎት በመስጠትና የአባ ጳውሎስን ህገወጥ ሲኖዶስ በመቃወም ለበርካታ አመታት ኖሯል። እንደ ሌላው የፖለቲካና ማህበራዊ ህይወትም የወያኔ መልዕክተኞች በውጭም ቤተክርስቲያንን በማወክና በመከፋፈል ብዙ ችግር ፈጥረዋል። ባለፈው ጽሁፌ ሳላነሳው የዘነጋሁት ነጥብ ስለሆነ እግረ መንገዴን ዳስሼው አልፋለሁ። በውጭ የሚገኘው ህጋዊ ሶኖዶስ ካለፉት ጥቂት ዐመታት ወዲህ ኢትዮጵያ ካለው የሀይማኖት አባቶች ጋር በመነጋገር እርቀሰላም እንዲወርድ ጥረት ቢደረግም የአባ ጳውሎስ ሰዎች በያዙት ገታራ አቋም ምንም ውጤት አላመጣም። በቅርቡም ደግሞ ከአገር ቤት ከመጡት ተወካዮች ጋር ስብሰባ ቢቀመጡም በውጭ ያሉት በአባ ጳውሎስ ሰዎች ፍላጎትና መንገድ ባለመሄዳቸው ያለስምምነት ተበትኗል። አሁን ደግሞ ሌሎች “ሽማግሌዎች” እርቅ እርቅ እያሉ በውጭ ከሚገኘው ሲኖዶስ ጋር እየተሞከረ መሆኑን እየሰማን ነው። በመሰረተ ሀሳቡ ሰላም፣ እርቅ ተፈላጊና መልካም ነገር ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ እውነተኛ እርቅ ለማድረግ የማይቻልበትና አደጋም ያለው ለመሆኑ በርካታ ፍንጮች አሉ። በውጭ ያለው “ተቃዋሚ” ነኝ እያለ መለስን በሌላ ለመተካት እየሸረበ ያለው ሴራ አንዱና ዋናው የሚፈልገው ነገር ይህን “እርቅ” ነው። የሃይማኖት አባቶች በቅንነትና በሰላም ፍለጋ “እሺ” ብለው ከተስማሙ፣ እነ “እገሌን” እንደ ታቦት አጅበው ከገቡ፤ “ብሄራዊ እርቅ ወረደ” ተብሎ በሚሊዮን የሚቆጠር ምእመናን እነርሱን ተከትሎ ካቀዱት ወጥመድ ውስጥ እንደሚገባላቸው፣ ይህም ሴረኞቹ ካቀዱት ዓላማ ጋር የሚስማማ ስለሆነ እሺ ለማሰኘት የማይላክ የሽማግሌ አይነት የለም፤ በውጭ የሚገኘው ሲኖዶስ ከዚህ እውነት ከመሰለ ሆኖም እጅግ አደገኛ የሆነውን መንገድ ባለማወቅና በስህተት እንደማይቀበሉት ከፍተኛ እምነት አለኝ። በወያኔው ጠ/ሚኒስቴር ታምራት ላይኔ ፓትርያርኩን ለማውረድ፣ ጳጳሳቶችን ለመከፋፈልና

በአንድ ላይ እንዳይቆሙ የሰራውን ግፍና ማታለል አይዘነጉትም። ወያኔ፣ አባ ጳውሎስና እሳቸው በመላው ቤተክህነት ያሰቀመጧቸው የአካባቢያቸው ተወላጅ ጀሌዎች እስካሉ ድረስ፣ መግባት ወይም መታረቅ ማለት ወደ ቄራ እንደሚነዳ የእርድ ሰንጋ መሆን ማለት ነው። ወያኔ እና አባ ጳውሎስ በኢትዮጵያ፣ በህዝቧ፣ በታሪኳና በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ያደረሱትን ከባድ ጥፋት ከሁሉም በላይ የሃይማኖት አባቶች ጠንቅቀው ያውቃሉ ብለን እናምናለን። አገር ያወቃቸው "ሽማግሌዎች" የሚባሉት እኮ የውጭና የወያኔ "መልዕክተኛ" እየሆኑ አይተናቸዋልና ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። አባቶች በእምነታቸው ጠንክረው ለዘለቄታ እውነተኛ ለውጥ ብቻ እንደሚታገሉ ደግሞ ጥርጥር የለውም እላለሁ። እግዚአብሄር ቀናውን መንገድ ያሳያቸው።

ሌላው በስደት የሚገኘው ኢትዮጵያዊ በግል ቤተሰቡን፣ ዘመዱን፣ ጎረቤቱን ጓደኛውን መርዳት ችሏል። በፖለቲካው አንጻር ግን አገር ቤት ያለውን ትግል ያግዝ እንደሆን እንጂ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርግ እንደሆን እንጂ፤ ትግሉን ከውጭ ሆኖ ለመምራት፣ ከውጭ ሆኖ መመሪያ ሊሰጥ አይችልም። ትክክልም አይደለም። ውጭ ተቀምጦ የ "ስደት መንግስት" ወይም "የሽግግር መንግስት" የሚባል ነገር ሊመሰርት አይችልም። ይህ ከኢትዮጵያ ህዝብ ትግልና ፍላጎት ውጭ ነው። አሁን እየተሞከረ ያለው ይህ አካሄድ እጅግ አደገኛና እውነተኛውን ትግል አቅጣጫ ለማሳትና አገራችንን የበለጠ ውስብስብ ችግር ውስጥ የሚከት ነው። በጽኑም እንቃወመዋለን።

ባለፈው ጽሁፌ እንደገለጽኩት፤ "ዳግማዊ ታላቁን ሴራ" ን ተግባራዊ ለማድረግ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና መሰሎቹ፣ እነ ስዬ አብርሃና ጓዶቹ ወዘተ… ዝግጅታቸውን አጠናቀው ሽር ጉድ ማለታቸው በውጭ የሚገኘው ሁሉ "በቃ ያሉን ተስፋ እነርሱ ናቸው፣ አሜሪካም ድጋፉን ሰጥቷቸዋል" በማለት ያሰፈሰፈው ሁሉ ረጋ ብሎ ህሊናውን መጠየቅ ይገባዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ የታገለው ለዚህ ነወይ? ያ ሁሉ ህዝብ ህይወቱን የሰዋበት፣ የታሰረበት፣ የተገረፈበት፣ የተሰደደበት እነዚህን ሰዎች ለማንገስ ነውን? የኢትዮጵያስ ህዝብ  የሚፈልገውንና የሚመራውን መንግስት የሚመርጥለት የውጭ መንግስት ነውን? ብሎ ራሱን መጠየቅና በማንቸገረኝና የአባትህ ቤት ሲዘረፍ … የሚለውን አስተሳሰብ ከህሊናው አውጥቶ ጥሎ፤ ኢትዮጵያ ያለው ቤቴን ንብረቴን ይቀሙኝ ይሆን? እያለ መዋለሉን ፣ መፍራቱን ትቶ፤  ከቻለ የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል ባገር ቤት ያግዝ፤ ካልቻለ ግን የጥፋት ተባባሪ ባለመሆን አርፎ ቢቀመጥ ትልቅ አስተዋጽኦ አደረገ ማለት ነው።

ከአስመራ ተነስቶ ኢትዮጵያን በ6 ወር ነጻ አወጣለሁ እያለ ቡራ ከረዩ ሲል የነበረው ብርሃኑ ነጋ እግረኛነቱን ትቶ "የአየር" ተዋጊ ሆነና "በሁለገብ ትግል ነጻ ማውጣቱ" ቀርቶ በሳተላይት ቲቪ "ነጻ" ሊያወጣን አታሞ መምታት ከጀመረ ሰነባበተ። ዛሬ "ኢሳት" የተባለው ሳተላይት ቴሌቪዥን እኮ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ኔትዎርክ (ETN) በመባል ሲተላለፍ ነበር። ይህ የተሟላ ዘመናዊ መሳሪያ ከነባለሞያዎቹ ከ "ሰማይ ዱብ ብሎ" ስራውን ከጀመረ በሁዋላ ስሙን በመቀየርና "ማነው ከጀርባ ያለው"? የሚለውን ለመደበቅና እንደው የሕዝብ ድጋፍ ያለው ለማስመሰል፤ "ለኢሳት መዋጮ አዋጡ" ይሉናል። ያለምንም ሀፍረት ኢሳትን በራሳችን አቋቋምን ሲሉ የሚያምን ካለ መቼስ ምን እላለሁ። እኔ ግን እዚችው ከተማዬ ውስጥ የሚሰራውን በሚገባ አውቃለሁና ዝም አልልም። ኤሮፕ ያሉ አንዱ ጋዜጠኛ እንኳን የኢሳት ገንዘብ ለነማን በገፍ እንደሚሰጥ ለነማን በጣም አነስተኛ ድጎማ እንደሚሰጥ በማየታቸው ራሳቸውን አግልለዋል። ቆራጥ!

ለመሆኑ ሰሞኑን በየከተማው የምናየው የጥምረትና የኦነግ ስብሰባ ሲል "ጥምረት" የተባለው እነማን ናቸው? ብንል በአጭሩ፤ አባል የሌለው ግን 7 መሪዎች ያሉት ግንቦት ሰባት፣  አቶ ነአምን ዘለቀ ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር በመሆን "የኢትዮጵያ ለአንድነትና ለፍትህ ንቅናቄ" የሚል ስያሜ ያወጣለት  "ድርጅት" ፤ ሌላው ደግሞ "የአፋር ህዝብ ፓርቲ" ተብሎ ብቸኛ መሪውም አባሉም የሆነው ካናዳ የሚኖር አቶ አሎ አይደሂስ የሚባል ሰው  ሲሆን፣ በአጠቃላይ 10 የማይሞሉ ሰዎች ያሉበትን እንደ ትልቅ የፖለቲካ ድርጅቶች "ጥምረት" ተብሎ አረፈው! መታወቅ ያለበት ዋናው ነገር ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ግን ምንም አይነት ግንኙነትም ሆነ መሰረት የሌለው መሆኑን መጤን አለበት! ጥምረት ነን ብለው ዶ/ር ብርሃኑ ሊቀመንበር፣ አቶ አሎ ምክትል፣ አቶ ነዐምንን ጸሀፊ

ተብሎ አዲስ ነጠላ ዜማ ተለቀቀ! ሌላ ዘፈን እስኪመጣ ድረስ በዚሁ ባለው መጨፈር ነዋ! ስደት ለወሬ ያመቻል አሉ። ይህቺ ነች ጨዋታ!

ጨዋታው ቀጠለ። ኦነግን በቅንጅት ጊዜ ተጻክሞና ተከፋፍሎ እስከነመኖሩም ተረስቶ፣ ከዚያም በሁዋላ ድምጹ ጠፍቶ እያለ፤ ብርሃኑ ነጋ (የህይወት ማቆያ እስትንፋስ ሰጥቶ) ከሞተበት ለማስነሳት ብዙ ዋተተ ፡፡ ጃንዋሪ 2012 ኦነግን ወደ "ኢትዮጵያዊነት" አመጣን አለን። ጉድ አይሰማ የለ ዘንድሮ ኦነግ ከአስመራ ሁኖ ኢትዮጵያዊነቱን አረጋገጠ! ኦነግ ከነፕሮግራሙ፣ ከነባንዲራው፣ ከነወነጀለኛ መሪዎቹ ተቀበሉ ተባልን! ላጠፋው የዘር ማጥፋት ወንጀል ምንም ነገር አታንሱ ተባልን። ዞሮ ዞሮ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዋና ዐላማ እንደ ወያኔ /ኢህአዴግ በዘር የተደራጁ ስብስቦችን ይዞ ኢትዮጵያን "ነጻ" ሊያወጣ ይኸው በአሜሪካ ከተሞች ሁሉ ስብሰባ በስብሰባ፣ የተናጋሪዎች ጠረጴዛ አባባ በአበባ፣ ግድግዳው ሁሉ በኦነግ ባንዲራዎች ተላብሶ፣ የስብሰባው ዜና የሳተላይት ቴሌቪዥንን ፕሮግራም ሲያጣብብ፣ በድህረ ገጾች ሲናፈስ ግራ የገባው ሁሉ "እረ ጉድ ልንሆን ነው ፣ ጥለውን ሊገቡ ነው እነዚህ ሰዎች" ብሎ አጀብ አጀብ ማድረግ ጀምሯል። በሬ ካራጁ ጋር መዋልና መላመድ ሲጀምር እንዲህ ነው! የአገሬ ሰው እኮ ተናግሮ ጨርሶታል፤

በሬ ሆይ በሬ ሆይ

ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ

እልም ካለው ገደል ገብተህ ቀረህ ወይ?

ብሎ ያለው ጥሩ ይገልጸዋል። ልብ ያለው ያስተውል።

ምንድነው ትልቁ አደጋና የሚያሰጋው ነገር? በ "መብት" ስም "በእኩልነት" ስም የዘር ድርጅቶች እንዲቀጥሉና እንዲጠናከሩ መደረጉና በ ሆነ "ተአምር" አቶ መለስ "ሲቀየሩ" ወይ "ስልጣን ሲለቁ" በእርግጠኛ ሌላ በዘር ፖለቲካ የሚያምን "ወያኔ ቁጥር ሁለትን" መተካቱን ለማረጋገጥ መጣራቸው ነው። አውቆ መታለል የፈለገ ይህን አባባል አለመቀበል ይችላል። እውነቱ ግን ይኸው ነው። እየሆነ ያለው ይህ ነው! ሆኖም ግን አትጠራጠሩ ይከሽፋል።

ኢትዮጵያ ጥንታዊትና ታሪካዊ አገር ናት። በወያኔ የዘር ጸበል የተጠመቁት እነ ብርሃኑ ነጋና ከማል ገልቹ አይደሉም ገና ወደፊት የሚመሰርቷት። እነ መለስ ዜናዊም እንዲያ እያሉ ሲያደነቁሩን ኖረዋል። ትግላችን እውነተኛ ዲሞክራሲን ማምጣት እንጂ በወያኔ የዘር ፖለቲካ መቀጠል ዳግም ጥፋት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር የሚፈታው በሀገሪቱ እውነተኛ ዲሞክራሲ ሲሰፍን፣ ህዝብ የመረጠው መንግስት ሲመሰረት፣ ህግ ሲከበርና ፍትህ ሲኖር፣ የሁሉም ባህልና ቋንቋ ሲከበርና ሲያድግ፣ ሁሉም ዜጋ በእኩልነት በመከባበር በፍቅር ሲኖር፣ ድንቁርና ረሃብና ድህነት ሲጠፉ፤ የብሄር ብሄረሰቦች ችግርም አብሮ ይፈታል፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆችዋ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!

ዋሽንግተን ዲሲ

ማርች 15 ቀን 2012